03

6ኛ ዓመት ቁጥር 7 6th year Nº 7	ባሕር ዳር መጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም Bahir Dar 27th March 2001

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 3.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	ፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.Box

ማውጫ	Contents
አዋጅ ቁጥር 53/1993 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የ1993 ዓ.ም በጀት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ገፅ 2	Proclamation Nº 53/2001 A Proclamation To Provide For The Amendment Of Amhara National Regional State 2000/2001 Fiscal Year Budget Proclamation Page 2

አዋጅ ቁጥር 53/1993 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የ1993 ዓ.ም በጀት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በመልክአ ምድራዊ ወሰኑ ውስጥ የክልሉን ሕዝብ ወክሎ የራሱን ገቢዎች የመሰብሰብ እና ዓመታዊ የሥራ ማስፈፀሚያ በጀቱን መርምሮ የማፅደቅም ሆነ የማሻሻል ሕገ-መንግሥታዊ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣

በዚህም መሠረት ለብሔራዊ ክልሉ የ1993 ዓ.ም መንግሥታዊ ሥራዎች ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ በጠቅላላው ብር 1,134,452,128 በጀት መስከረም 24 ቀን 1993 ዓ.ም ባደረገው መስራች ጉባኤ መክሮ ያፀደቀ ቢሆንም ከዚህ ውሳኔው በኋላ ከፍ ብሎ

Proclamation Nº 53/2001
A proclamation to provide for the amendment of the Amhara National Regional State 2000/2001 Fiscal year Budget proclamation

WHERE AS, the council of the Amhara National Regional State is constitutionally empowered to collect its own Revenues and thereby approve or amend its annual budget to execute governmental undertakings within the limit of its own geographical boundary duely representing the people of the region.

WHERE AS, though the amount of the National Regional State 2000/2001 Fiscal year budget appropriation for governmental undertakings which was deliberated upon and approved by the Amhara National Regional council during its founding congress held on octover 4th 2000 happened to reach birr 1,134,452,128 (one billion, one hundred thirty four million, four hundred fifty two thousand and one hundred

በተጠቀሰው የፀደቀ በጀት ላይ የመጠን ለውጥ የሚያስከትል ሁኔታ የተከሰተ በመሆኑ፣

የክልሉ ም/ቤት በብሄራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.1 እና 9 ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን የበጀት ጣሪያ ማሻሻያ አዋጅ አውጥቷል::

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የ1993 ዓ.ም የመንግሥት ሥራዎች ማስፈፀሚያ በጀት አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 53 /1993 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ማሻሻያ

የ1993 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራዎች ማስፈፀሚያ በጀት አዋጅ ቁጥር 52/1993 ዓ.ም ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተስተካክሏል::

በ1993 ዓ.ም በጀት አዋጅ መሠረት፣

ሀ/ ከውጭ ብድር ይገኛል ተብሎ ከሚጠበቀው ብር 192,920,000 ውስጥ ለመስኖ ልማት ድጋፍ ተይዞ የነበረው ብር 19,780,000 እና፣

ለ/ከውጭ እርዳታ ይገኛል ተብሎ ከሚጠበቀው ብር 84,690,000 ውስጥ ለባሕላዊ መስኖ ልማት ማስፋፊያ ተይዞ የነበረው ብር 3,180,000 በፌዴራሉ መንግሥት አማካኝነት የተያዙ ስለሆነ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት በጀቶች ድምር ብር 22,960,000 በዚህ አዋጅ መሠረት አስቀድሞ ከፀደቀው የክልሉ ጠቅላላ ዓመታዊ በጀት ላይ ተቀናሽ እንዲሆንና ዓመታዊ የ1993 ዓ.ም የክልሉ መንግሥት የበጀት ጣሪያ ብር 1,134,452,128 መሆኑ ቀርቶ ብር 1,111,492,128 ተብሎ እንዲስተካከል ተወስኗል::

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባሕር ዳር
መጋቢት 18 ቀን 1993 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

twenty eight) in total, a situation has now been created so as to necessitate an alteration in amount after its earlier decision to approve the grand budget indicated hereof;

NOW, THEREFORE, the Regional Council, by virtue of the powers vested in it under article 49 sub art. 3/1 and 9 of the National Regional Constitution, hereby proclaims the budget ceiling amendment proclamation as follows.

1. Short Title

This proclamation may be cited as "the 2000/2001 fiscal year governmental undertaking executionary budget amendment proclamation No 53/2001".

2. Amendment

The Amhara National Regional State 2000/2001 fiscal year governmental undertakings executionary budget proclamation No 52/2000 is hereby amended and adjusted as indicated bellow.

It is hereby found out that the following two budget items contained in the grand budget of the region are already indicated under the federal Government current budget proclamation and hence held to be reduced out of the total grand National Regional State Fiscal year budget proclamation hereof.

A/ 19,780,000 (Birr Nineteen million seven hundred eighty thousand) appropriated for an irrigation development support which was then expected to be drawn from foreign loan worth birr 192,920,000 (One hundred ninety two million nine hundred twenty thousand);

B/ 3,180,000 (Birr three million one hundred eighty thousand) appropriated for traditional irrigation development expansion, which then expected to be drawn from the foreign loan worth Birr 84,690,000 (Eighty four million six hundred ninety thousand); In effect, it is hereby decided by this proclamation that the above indicated budget items, an aggregated amount of which reaches birr 22,960,000 (twenty two million nine hundred sixty thousand), be reduced out of the grand annual budget formerly proclaimed to total birr 1,134,452,128 (one billion, one hundred turity four million four hundred fivity two tuthend and one hundred twenty eight). And the ceiling of the actual grand budget of the 2000/2001 fiscal year accordingly, instead, stand to be birr 1,111,492,128 (One billion one hundred eleven million four hundred ninety two thousand and one hundred twenty eight).

3. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the 27th day of March 2001.

Done at Bahir Dar
This 27th day of March 2001
Council of the Amahara National Regional State